metro

ነሀሴ 4 ቀን 2017 ዓ.ም.

ውድ ቤተሰብ/አሳዳጊ፣

ሜትሮን በመወከል፣ ለአዲስ የትምህርት ዓመት የጋለ ስሜትን እናካፍልዎታለን። ተማሪዎ ለDCPS እና PCS ተማሪዎች እና ለግል እና የኃይማኖት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሜትሮ-አውቶቡስ እና ሜትሮ-ባቡር በነፃ መሳፈር የሚያስችል አስፈላጊ የመጓጓዣ ጥቅም እንዲሳተፍ እባክዎ የልጆች ነፃ መሳፈሪያ ፕሮግራም ጋር እራስዎን ያስተዋውቁ።

**በአውቶቡስ እና በባቡር ለመሳፈር እያንዳንዱ ተማሪ የዲስ ዋን ካርድን ወይም ስማርትሪፕ ካርድን የዋጋ ሳጥን/በር ላይ መንካት አለበት። በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ልጅዎ በልጆች ነፃ መሳፈሪያ ፕሮግራም መካፈላቸውን ለማረጋገጥ፣ እባክዎን እነኚህን መመሪያዎች ያንቡ።**

በእነኚህ ቀላል ደረጃዎች መተላለፊያውን በዲሲ ዋን ካርዱ ላይ ይጫኑ።

1. በሜትሮ-ባቡር ጣቢያ ወይም በማንኛውን አውቶቡስ ላይ <u>የዲሲ ዋን ካርዱን በዋጋ ሳጥኑ መሣሪያ ላይ ያስነኩ</u>። ከ$0 በታች ቀሪ ካሳየ ወደ $0 ያድርሱት።
2. ካርዱ በሜትሮ ባቡር ጣቢያ ከስድስት ሰዓት በኋላ ወይም በሚቀጥለው ቀን ከተነካ መተላለፊያውን ለመጫን <u>እዛው ጣቢያ ተመልሰው ካርዱን በዋጋ ሳጥን መሣሪያ ላይ ያስነኩ</u>።
3. ካርዱ በሜትሮ-አውቶቡስ ላይ ከተነካ፣ ፈቃዱን ለመጠቀም ሦስት የሥራ ቀናት ይጠብቁ። <u>ፈቃዱ መጫኑን ለመጨረስ ካርዱን እንደገና በሜትሮ አውቶቡስ የዋጋ ሳጥን ላይ ያስነኩ</u>። ፈቃዱ እስከሚጫን ድረስ፣ በሜትሮ-አውቶቡስ ወይም ሜትሮ-ባቡር ለመሳፈር ተማሪዎች በዲሲ ዋን ካርዳቸው ላይ ገንዘብ መጨመር አለባቸው።

የዲሲ ዋን ካርድ <u>በዲስትሪክቱ ውስጥ</u> እና አምስት አዋሳኝ ጣቢያዎች (ሲልቨር ስፕሪንግ፣ ፍሬንድሽፕ ሀይትስ፣ ካፒቶል ሀይትስ፣ ሳውዘርን አቨኑ እና ኔይለር ሮድ) ለትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ጋር ለተያያዙ እንቅስቃሴዎች በነጻ የመሳፈር አገልግሎት ይሰጣል። ተማሪዎች ከእነኚህ አዋሳኞች ውጭ ቢጓዙ፣ በዲሲ ዋን ካርዳቸው ላይ ያጠራቀሙትን ገንዘብ ይጠቀማሉ። <u>በካርዱ ላይ የተጠራቀመ ገንዘብ ከሌለ፣ ቀሪው ከ$0 በታች በመሆን የልጆች ነጻ መሳፈሪያ ፈቃዳቸውን ከሥራ ውጭ ያደርገዋል</u>። አንዴ ቀሪው ወደ $0 (ወይም በላይ) ከተመለሰ፣ ተማሪው የልጆች ነጻ መሳፈሪያ ፈቃድን መጠቀም ይችላል።

የሜትሮ የጉዞ ፖሊስ መምሪያ የዋጋ ማጭበርበርን ለማቆም ይሠራል፣ ይህም ማለት፣ ሁሉም ተሳፋሪዎች ካርዳቸውን በባቡር እና አውቶቡስ ላይ ማስነካት አለባቸው። የዲሲ ዋን ካርድ ያላቸው ተማሪዎች ካርዳቸውን ካልያዙ፣ በዋጋ ሳጥኑ ላይ ማስነካት ወይም የስማርትሪፕ ካርድ በመጠቀም ሙሉ ዋጋ መክፈል አለባቸው።

ልጅዎ ነጻ የሜትሮ ጉዞ አገልግሎት ጥቅሞችን እንዲያገኝ እባክዎ የልጆች ነጻ መሳፈሪያ ፈቃድን እንዲጭን ጊዜ ወስደው ይርዱት። ችግሮች ወይም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ kidsridefree.dc.gov ድህረ ገጽን ይጎብኙ ወይም ለDDOT ትምህርት ቤት ጉዞ ድጋፍ ፕሮግራም ቢሮ በ(202) 673-1740 ይደውሉ።

በዲሲ ዋን ካርድ የተጫነውን የልጆች በነጻ መሳፈሪያ ፈቃድን በመያዝ፣ ልጅዎ ለሌላ አሳታፊ እና ስሜትን የሚቀሰቅስ የትምህርት ዓመት ዝግጁ ነው!

ከምስጋና ጋር፣

Ronald A Pavlik Jr

**ሮናልድ ኤ. ፓቭሊክ ጁኒየር**

የፖሊስ ኃላፊ፣ ሜትሮ የጉዞ ፖሊስ መምሪያ
የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን አካባቢ የጉዞ ባለሥልጣን

**Washington Metropolitan Area Transit Authority**

600 Fifth Street, NW
Washington, D.C. 20001
202/962-1234

*By Metrorail:*
*Judiciary Square-Red Line*
*Gallery Place-Chinatown*
*Red, Green and Yellow Lines*

*A District of Columbia Maryland and Virginia Transit Partnership*